# በጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ አዎንታዊ ውሳኔ ሲያገኙ

**በጥገኝነት ጥያቄዎ ላይ አወንታዊ ውሳኔ ከተቀበሉ በኋላ ምናልባት ብዙ የሚያስቡበት ነገር እንዳልዎት እናውቃለን። እነዚህም የመማር፡ የመስራት ወይም የምታስቡላቸውን ሰዎች ለማየት የመጓዝ እቅድዎን ሊያካትቱ ይችላሉ። ውሳኔዎን ከተቀበሉ በኋላ የጥገኝነት ድጋፍዎ ከማብቃቱ በፊት ትንሽ ጊዜ ብቻ ነው የሚኖርዎት ስለዚህ በመጀመሪያ በእነዚህ ሶስት ነገሮች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው።**

## 1. የሁኔታ እና የመታወቂያ ማረጋገጫ - የእርስዎ ባዮሜትሪክ መኖሪያ ፍቃድ (BRP)

- አዎንታዊ ውሳኔ ካገኙ በኋላ፡ ሆም ኦፊስ ለእርስዎ ወይም ለጠበቃዎ የ BRP ካርድ መላክ አለበት። በኢሜል ወይም በፖስታ ሊመጣ ይችላል። ይህንን የመኖሪያ ቦታዎን ለቀው ከመውጣትዎ ቢያንስ ከ7 ቀናት በፊት ማግኘት አለብዎት።
- BRP አዲሱ የመታወቂያ ሰነድዎ (መታወቂያዎ) ነው እናም በጣም አስፈላጊ ነው። ስራ ለማግኘት ወይም ጥቅማጥቅሞችን (ቤነፊት) ለመጠየቅ እና የመኖሪያ ቦታ ለመከራየት ያስፈልግዎታል።
- የ BRP ካርድ ካልተቀበሉ እና ድጋፍዎ በ 7 ቀናት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ የሚያበቃ ከሆነ፡ እባክዎን በአስቸኳይ ማይግራንት ሀልፐን በ 0808 8010 503 ወይም positivemoveon@migranthelpuk.org ያግኙ።

## 2. ገንዘብዎ

- አወንታዊ ውሳኔ ካገኙ በኋላ ሰርተው ገንዘብ እንዲያገኙ ይፈቀድልዎታል።
- መስራት ካልቻሉ ወይም ስራ በፍጥነት ማግኘት ካልቻሉ፡ ለደህንነት ጥቅማጥቅሞች (በተለምዶ ዩኒቨርሳል ክሬዲት) ማመልከት አለብዎት። በኦንላይን ላይ ወይም በአከባቢዎ በሚገኘው ጆብ ሴንተር ፕላስ በአካል በመቅረብ ማመልከት ይችላሉ።
- ክፍያዎችዎን ከመቀበልዎ በፊት የተወሰነ ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል ይህን ወዲያውኑ ያድርጉ።
- BRP ከሌለዎት፡ ጥገኝነት እንደተሰጥዎት የሚያረጋግጠው ደብዳቤዎን እና የARC ካርድዎን በመጠቀም ለደህንነት ጥቅማጥቅሞች ማመልከት ይችላሉ።
- የባንክ ሂሳብ መክፈትም ያስፈልግዎታል።

## 3. የመኖሪያ ቤትዎ

- አወንታዊ ውሳኔ ካገኙ በኋላ፡ የራስዎን መኖሪያ ቤት መፈለግ መጀመር እና ወደዛም መሄድ ይችላሉ።
- የአካባቢዎን አስተዳደር (ውሳኔዎን ሲያገኙ ሚኖሩበት የነበሩበት ቦታ) እርስዎን እንዲረዳዎ መጠየቅ ይችላሉ። በአጠቃላይ ጤነኛ ከሆኑ እና ከእርስዎ ጋር የሚኖሩ ልጆች ከሌሉዎት ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት ሰው አይታዩም እና ምንም አይነት ማረፊያ ቤት ሊሰጡዎት አይችሉም። በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም ሰው ከፍተኛ የማህበራዊ መኖሪያ ቤት እና የካውንስል ቤት እጥረት አለ።

### የመኖሪያ ቤት ኤቢሲ (ABC)

A መጀመሪያ - የሚያገኙት የመጀመሪያ ቦታ ለአጭር ጊዜ ብቻ ሊሆን እንደሚችል **ይቀበሉ**። ምናልባት ትንሽ፡ የጋራ ወይም ጊዜያዊ መጠለያ እንጂ መኖር በሚፈልጉት አካባቢ ላይሆን ይችላል።

B ቀጥሎ - የተወሰነ ገቢ እና/ወይም ስራ ካገኙ በኋላ፡ ወደሚፈልጉበት ቦታ ቅርበት ያለው፡ ነገር ግን ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ **የተሻለ** ቦታ መፈለግ ይችላሉ። እንደ የእንግሊዘኛ ትምህርት እና የቅጥር ድጋፍ ያሉ ነገሮች ይህን ለማድረግ ይረዱዎታል።

C በኋላ - ለረጅም ጊዜ መኖር ወደሚፈልጉት **ምቹ** ቤትን ለማግኘት ይስሩ።

SCAN ME

RSMP NORTH WEST REGIONAL STRATEGIC MIGRATION PARTNERSHIP

boaztrust

በአካባቢዎ ስላለው እገዛ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ድህረ ገጽ ለመክፍት የስልክ ካሜራዎን በዚህ ኪው አር (QR) ኮድ ላይ ይጠቁሙ።